# የነፃነት ትግላችን ዘላቂ እንዲሆን

## - ጋሻ ለኢትዮጵያውያን




“የኤርትራ ህዝብ ሆይ! ለነፃነት ስትሉ ከፍተኛ መስዋእትነት ከፍላችሁ፣ ነፃነታችሁን ተቀዳጀችሁ። መላው የዓለም ህብረተሰብም ነፃነታችሁን አወቆ አፀደቀላችሁ። እንኳን ደስ ያላችሁ! ዛሬ የኤርትራ ህዝብ አንድ የታሪክ ምዕራፍ ዘግቷል። ያ ምዕራፍ ምን አይነት እንደነበር የጉዳዩ ባለቤት ለእናንተው ለማስረዳት አልሞክርም። ለምን? ቁስል እንዳላችሁ አውቀዋለሁ። ለምን? ቁስላችሁን ከቅርብም ሆነ ከሩቅ ሆኜ ስለማውቀው ነው። ለምን? በእኔ ጀርባና በእናንተ ጀርባ ላይ አንድ አይነት ቁስል እንዳለ ስለማውቅ ነው። ያም ሆኖ ጉዳዩ አልቋል። ጠላት ተቀብሯል፡፡ ሰዎች ብቻ አይደለም የቀበርነው፤ አመለካከትም ጭምር ነው። አስተሳሰብም ጭምር ነው የቀበርነው።” — (መለስ ዜናዊ በግንቦት ወር 1994 እ.ኤ.አ. አስመራ ስታድዮም ለተሰበሰብ ህዝብ ካደረገው ንግግሩ የተወሰደ።)

* * * * *

“የኤርትራ ህዝብ ከኢትዮጵያ ቅኝ አገዛዝ ወደር የሌለው መስዋእትነት ከፍሎ ነፃነቱን ያጎናፀፈው ድርጅት ህወሓት ወያኔ ነው። አሁንም አያርገውና የኤርትራን ነፃነት የሚፈታተን ኃይል ከተነሳ፣ ኤርትራ በወራሪ ኃይል ጦርነት ከተከፈተባት፤ በኢህአዴግ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግስት እጆቹን እጣጥፎ ይቀመጣል የሚል እምነት የለኝም። ጦሩን ሰብቆ ኤርትራ ገብቶ ከኤርትራ ህዝብ ጎን ቆሞ የኤርትራን ጠላት እንደሚመክት ቅንጣት ታክል አልጠራጠርም።” - ስብሃት ነጋ (ከፍተኛ የወያኔ/ኢህ አዴግ ባለስልጣን ግንቦት 28 ቀን 2007 ከወያኔ ሬድዮ ጋር ሁለት ሰዓት ተኩል ከፈጀ ዲስኩሩ የተወሰደ።)

* * * * * *

አበው ሲተርቱ፣ “አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ” ይላሉ። በኢትዮጵያ የመንግስት ስልጣን ተቆጥጥሮ ለ16 ዓመት ሙሉ ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ‘የአካዳሚክ ነፃነት የይከበርልን” ከሚል እጅግ መሰረታዊ ጥያቄ እስከ በህዝብ ምርጫ ለመንግስት ስልጣን ተወዳድሮ ለአሸነፈው የቅንጅት ድርጅትን በጥይት እያስተናገደ፣ የኢትዮጵያን ተስፋ አጨልሞ ያለው ኃይል ማን ነው?

አዎ፣ ማነው?

ህወሓት/ኢህአዴግ የተባለው ገዢ ቡድን “ወያኔ” በሚል የአጭበርባሪዎች ካባ አጥልቀው በኤርትራ ውስጥ ሲካሄድ የነበረውን የማስገንጠል ጦርነት ለማገዝና ማዕከላዊው የኢትዮጵያ መንግስትን ገልብጠው ስልጣን ለመያዝ ባሴሩ ቅጥረኞች የሚመራ ድርጅት ነው።

ይህ ቡድን የኤርትራን መገንጠል፣ የኢትዮጵያ የቀይ-ባህር ክልልዋ ማጣትና ወደብ አልባ መሆን፣ የአፋር ክልል ህዝባችን መበታተንና ኢትዮጵያዊ ዜግነቱ ማጣት ጥያቄ ውስጥ ያስገባ ፍጡር ሁሉ ሲያስር፣ ሲያሳድድና ሲገድል የኖረ ነው።

### <u>መለስ ዜናዊ ስልጣኑን ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠሩ አደገኛነት</u>

ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር ያደረገችው ጦርነት በድል ዋዜማ ላይ እያለች መለስ ዜናዊ ደርሶ እንዳከሸፈው ይታወቃል። በዚሁ ወንጀል የተናደዱት ዛሬ በእስር ቤት የሚማቅቁት ስዬ አብርሃና ጓደኞቻቸው መለስን በአገር ክህደት ወንጀል ለመክሰስ ሲዘጋጁ፣ ቀድሞውኑ ይህ አደጋ ይመጣብኛል ብሎ አድብቶ ሲጠባበቅ የነበረው የህወሓት የኤርትራ ክንፍ ቅፅበታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ባለጋራውን በፖለቲካ ብትር አሽመድምዶ ከጨዋታው ውጭ ማድረጉ ይታወሳል።

ይህ ድል የኤርትራ ባላደራ መንግስት መሪ ለሆነው አቶ መለስ ዜናዊ የመንግስት ስልጥንን በሚያሰፈራ መልኩ እንዲቆጣጠር አስችሎታል። ኢትዮጵያ በማን እጅ እንደወደቀች ላለማስታወቅ ሲል፣ ወዲያውኑ የተንኮል መረቡን በመዘርጋት በ "ዲሞክራሲ" እና "ነፃ ምርጫ" በሚሉ ማራኪ ቃላቶች የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ቡድኖችን ትኩረት ስቦ ለአራት አመታትም ሲንቀሳቀስበት ቆይቷል። ጨዋታው ግን ከታሪካዊው ከግንቦት 7 ቀን 1997 ዓ.ም. ምርጫ ሊያልፍ አልቻለም። የኢትዮጵያ ህዝብ የባዕድ አገዛዝ በቃኝ በማለት ለተቃዋሚዎች ፖርቲ ያለውን ሙሉ ድጋፍ ሰጥቷል።

ከተቋቋሙ በጥቂት ወራት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ እምነት ሊያገኙ የቻሉት ህብረትና በተለይም ቅንጅት የመለስ ዜናዊ ቡድንን በሚያሳፍር መልኩ አሸንፈዋል። ቅንጅት በአዲስ አበባ ትልቅ ድል ተጎናፅፎ ተጨማሪ ድሎች እየተጠባበቀ በነበረበት ወቅት፣ ሽንፈቱን ወለል ብሎ የታየው ቡድን የአስቸኳይ ጊዜያዊ አዋጅ በመደንገግ በ24 ሰዓት ውስጥ ኢትዮጵያን ከዲሞክራሲያዊ ጎደና ገፍትሮ ወደ ፈላጭ-ቆራጭ አምባገነናዊ አገዛዝ የወረወራት።

ስልጣኑን ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ላለማስረክብና የኤርትራ ነፃነት ባላደራነቱን ለማስጠበቅ በኢትዮጵያ የተቃዋሚ መሪዎችና ደጋፊዎች፣ ጋዜጠኞችና የሰብአዊ መብት ጠባቂዎች ላይ የግድያ፣ የእስራትና በአጠቃላይ የሽብር አገዛዝ በሰፊው ከፍቶ በሰፊው ሲንቀሳቀስበት ቆይቷል።

በቅርቡ በቅንጅት መሪዎችና ጋዜጠኞች ላይ የተላለፈው ብይን የሚያረጋግጥልን ነገር ቢኖር፣ ገዢው ፓርቲ ምን ያህል የኢትዮጵያ ህዝብ መብት ረግጦ አገሪቱን መቀመቅ ውስጥ ከትቶ ለመኖር ቆርጦ እንደተነሳ ያረጋግጥልናል። አመቺ መስሎ ሲታየው ደግሞ፣ የተቃዋሚ መሪዎችን እንደዛ ከመሰለ ወንጀል አላቆ ስልጣኔን አትንኩ እንጂ ልፈታችሁ እችላለሁ ።

ጋሻ ለኢትዮጵያውያን የቅንጅት መሪዎች ከእስር መፈታት በፀጋ ይቀበላዋል። ቀድሞውኑም ቢሆን የቅንጅት "ወንጀል" ለፓርላማ ተወዳድሮ ማሸነፉ ነው። ስለዚህ እነኚህ አንጋፋ የቅንጅት መሪዎች ከዘግናኝ የቃሊቲ እስር ቤት መለቀቅ ትልቅ የኢትዮጵያ ህዝብ ድልና ደስታ ነው ይላል።

ሆኖም ግን ለ16 ዓመታት የዘለቀው አፈናና ሽብርተኘነት በቅንጅት አባላትና ደጋፊዎች ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፣ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ፣ ለበርካታ አመታት ታስረው፣ አስታዋሽ ያጡ የፖለቲካ እስረኞችም ይመለከታል። እነዚሁም ወገኖች የነፃነት አየርን የማይተነፍሱበት ምንም ምክንያት የለም። የቅንጅት መሪዎች መፈታት በሌላ የፖለቲካ ብትር እስከንመታ ድረስ የተወሰደ ጊዜያዊ እርምጃ እንዳይሆን በንቃት መከታተል አለብን። ኢትዮጵያ ነፃ ሆናለች ለማለት የምንችለው የህዝቡ የዲሞክራሲ መብቶች፣ የፕረስ ነፃነትና የህግ የበላይነት ሲከበሩ ብቻ ነው። ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ አሁንም ለዲሞክራሲና ለፍትህ የሚደረገው ትግል ተጠናክሮ የቀጠለ እንደሆነ ነው። በዚህ የነፃነት ትግል ደግሞ ጋሻ ለኢትዮጵያውያን የዜግነት ድርሻውን እንደሚወጣ እምነቱ የፀና ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!

ጋሻ ለኢትዮጵያውያን
ዋሽንግተን ዲሲ
ሰኔ 21 ቀን 2007